**የፎቅ ታወርስ ክፍል እርምጃ**

**ኢድሪስ ሃሳን**

**እና**

**የሀዋ ዋርሳም**

**ከ**

**ክፍለ ከተማ ቪክቶሪያ**

**(S ECI 2021 00826)**

# የታቀደው የስምምነት መፍትሄ ማሳሰቢያ

**እባክዎ ይህን ማሳሰቢያ በጥሞና ያንብቡና ተጨማሪ እርምጃ መውሰድ ካስፈለግዎትና ካላስፈለገ መገንዘብ። ይህ ማስታወቂያ ህጋዊ መብቶችዎን ሊነኩ የሚችሉ መረጃዎችን የያዘ ጠቃሚ ሰነድ ነው።**

**1. ይህን ማሳሰቢያ የደረስዎት ለምንድን ነው?**

መጋቢት/March 19 ቀን 2021 ዓ.ም. አቶ ኢድሪስ ሐሰንና ወይዘሮ ሐዋ ዋርሳም (**ከሳሾች**) በከፍተኛ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለክፍል እርንጃ ጥያቄ እንደጀመሩና (**ሂደቱ እንደቀጠለ**) ይህም በአስተዳደር ግዛት ላይ የቀረበ ክስ ለመዋጋት (**አቃቤ ህግ**) ላይ የክፍሌ የቅጣት አቤቱታ አስጀመሩ።

- በአድራሻ Pampas Street, 159 Melrose Street, 33 Alfred Street, 76 Canning Street እና 12 Sutton Street, North Melbourne, እና 120,126 እና 130 Racecourse Road እና 12 Holland Court, Flemington/ፍሌሚንግተን (**መኖሪያ እርስት ስቴት ታወርስ**) ከቀን 4 እስከ 9 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም ድረስ፤ እና

- ከቀን 10 እስከ 18 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በኖርዝ ሜልቦርን ፎቅ አድራሻ 33 Alfred Street የሰዎች 'መዝጋት' እንደቀጠለ ነው።

የፍርድ ሂደቱን ያቀረቡት በራሳቸው፣ እንዲሁም ተመሳሳይ ጥያቄ ያላቸውን ሌሎች ሰዎች በመወከል (**የቡድን አባላት**) ነው።

ከሳሽ እንዳሉት ተከሳሽ፡

(a) በሐምሌ/July 2020 ዓ.ም ከሳሽና ቡድን አባላት በስህተት እስከ 14 ቀን ድረስ በቁጥጥር ሥር እንደዋሉ፤ እና

(b) ከሳሾችና የቡድን አባላት ሕንጻውን ለቅቀው ለመውጣት ከሞከሩ አካላዊ ጉዳት እንደሚያደርሱባቸው በተሳሳተ መንገድ አስፈራሯቸው።

ተከሳሹ እነዚህን አባባል ክሶች ይክዳል።

ከሳሽና ተከሳሽ ያለ ፍርድ ቤት ክርክር በጋራ ድርድር ለመፍታት ስምምነት ላይ ደርሰዋል። የቀረበው መፍትሄ ውሳኔ ተግባራዊ የሚሆነው ፍርድ ቤቱ ከፈቀደለት ብቻ ነው ። የቀረበው ስምምነት ፈቃድ ካገኘ፤ የቡድን አባላትን መብቶች ይነካል።

ይህ ማሳሰቢያ የቡድን አባላት ሊሆኑ ለሚችሉ ሰዎች መረጃ ለማግኘት እንዲችሉ እንዲታተም ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል። የቡድን አባል ስለሆናችሁ ይህንን ማሳሰቢያ እየደረሳችሁ ነው።

**2. ይህ ማሳሰቢያ ምንድን ነው?**

ይህ ማሳሰቢያ ስለቀረበው መፍትሄ ውሳኔ ጠቃሚ መረጃዎችን ይዟል፤ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

(a) የቡድን አባል መሆን አለመሆንዎን እና በቀረበው የስምምነት ላይ ለመሳተፍ ብቁ መሆንዎን እንዴት መወሰን ይቻላል፤

(b) የታቀደው የመፍትሄ ስምምነት ቅድመ ሁኔታ እና በቡድን አባላት ላይ እንዴት እንደሚሰራ፤ እና

(c) ከፈለጉ ምን ማድረግ አለብዎት፡

i. **በቀረበው መፍትሄ ስምምነት ላይ ለመሳተፍ** መመዝገብ፤

ii. **ከቀረበው መፍትሄ** መርጠው በአሰራሩ ሂደት ውስጥ የቡድን አባል ስለመሆን ማቆም፤ ወይም

iii. **ለቀረበው መፍትሄ ስምምነት መቃወም** ።

***ይህን ማሳሰቢያ በጥንቃቄ ማንበቡ አስፈላጊ ሲሆን ምክንያቱም ይህ ማሳሰቢያ ማድረግ ያለብዎትን መረጃ የያዘ እና መብትዎን ሊነካ ስለሚችል ነው።***

በዚህ ማሳሰብያ ውስጥ ያልተረዳዎት ነገር ካለ ወይም ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የከሳሹን የህግ ተወካይ፤ Clemens Haskin Legal በስልክ (03) 9988 5035 ማነጋገር ወይም በኢሜይል info@clemenshaskin.com መገናኘት ወይም የራስዎን የህግ አማካሪ መጠየቅ ይኖርብዎታል።

በሌላ ቋንቋ የዚህን ማሳሰቢያያ ግልባጭ ከፈለጉ ቅጅዎች በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ በካንቶኒዝ፣ በዳሪ፣ በዲንቃ፣ በፋርሲ፣ በፋርሲ፣ በማንዳሪን፣ ኦሮምኛ፣ ሶማሌኛ፣ ትግርኛ፣ ባህላዊ ቻይንኛ፣ ቱርክኛና ቬትናምኛ በድረገጽ health.vic.gov.au/covid-19-towers ላይ ከቀን 10 ግንቦት/May 2023 ዓ.ም ጀምሮ ይቀርባል።

በቀን 27 ሰኔ/ June 2023 እድሚዎ ከ18 ዓመት በታች ከሆነ ወይም ጉዳያችሁን በማስተዳደር ረገድ በጉዳት፣ በበሽታ፣ በእርጅና፣ በህመም ወይም በአካል ወይም በአእምሮ አእምሮ ህመም ምክንያት አቅም ከሌለዎት ከአሰራር ሂደቱ ጋር በተያያዘ (**በአካል ጉዳተኛ ስር ላለ ሰው**) እባክዎ ይህን ማሳሰቢያ

ለመጉዚት ጠባቂዎ ወይም ለግል ተወካይዎ (ካለዎት) ያቅርቡለት። የአካል ጉዳተኛ መሆን አለመሆንህን እርግጠኛ ካልሆንክ ለ Clemens Haskin Legal/ክሌመንስ ሃስኪን ሊጋልን ማነጋገር ወይም ለራስዎ የህግ ምክር ልትጠይቅ ወይም ሌላ ሰው እንዲፈለግልዎት ሊያደርጉ ይችላሉ።

**3. የቡድን አባል ማነው?**

በቦታው ከነበሩወይም ከቆዩ የቡድን አባል መሆን የሚችሉት፡

(a) ከዚህ በሚከተሉት አንደኛው አድራሻ ከነበሩ ነው፡

i. 12 Holland Court, Flemington 3031;

ii. 120 Racecourse Road, Flemington 3031;

iii. 126 Racecourse Road, Flemington 3031;

iv. 130 Racecourse Road, Flemington 3031;

v. 9 Pampas Street, North Melbourne 3051;

vi. 12 Sutton Street, North Melbourne 3051;

vii. 33 Alfred Street, North Melbourne 3051;

viii. 76 Canning Street, North Melbourne 3051;

ix. 159 Melrose Street, North Melbourne 3051;

(በጋራ ከ**Estate Towers**) ፎቆች ጋር; እና

(b) ከሚከተለው በማንኛውም ጊዜ፡

i. ሐምሌ/July 4 ቀን 2020 ዓ.ም (ወይም ከዚያ በኋላ ብዙም ሳይቆይ) ከምሽቱ 4 00 pm ወይም 4 30 pm ሰዓት ገደማ እስከ ሐምሌ/July 9 ቀን 2020 ዓ.ም እስከ 5 00 pm ሰዓት ድረስ (በአድራሻ 9 Pampas Street, North Melbourne እና 159 Melrose Street, North Melbourne ላይ በተፈጠረ) እና ሐምሌ/July 4 ቀን 2020 (ወይም ከዚያ ብዙም ሳይቆይ) ከምሽቱ 4 pm ሰዓት ወይም ከምሽቱ ከ4 30 pm ሰዓት ገደማ በኋላ ሐምሌ/July 9 ቀን 2020 እስከ ምሽቱ 11 59 pm ሰዓት ድረስ በሌሎች ንብረቶች ህንጻዎች ሁሉ ላይ፤ ወይም

ii. ከምሽቱ 11.59 pm እስከ ቀን 9 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም እስከ ምሽቱ 11:59 pm በቀን 18 ሐምሌ/July 2020 ዓ.ም በአድራሻ 33 Alfred Street, North Melbourne ላይ በተፈጥረ ጉዳይ።

**4. የታቀደው መፍትሄ ስምምነት ምንድ ነው?**

ከሳሽና ተከሳሽ የክሱን አሰራር ሂደት እልባት ለመስጠት ተስማምተዋል። የቀረበው መፍትሄ ውሳኔ በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት ካገኝ የፍርድ ሂደቱ በስምምነት ይፈታል፤ የፍርድ ችሎትም አይካሄድም።

የታቀደው የመፍትሄ ስምምነት ዋና ቁልፍ አገላለጽ የሚከተሉት ናቸው፡

(a) ተከሳሽ የአምስት ሚሊዮን ብር ($5,000,000.00 ዶላር) (**ጠቅላላ ለመፍትሄ ስምምነት**) ይከፈለዋል፤

(b) ከሳሾች ባላቸው አቋም ሁኔታ ግምት በማስገባት ከጠቅላላ የመፍትሄ ስምምነት መጠን እንዲቀነስ ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችሉ ይሆናል፤ ይህም የቡድን አባላትን በመወከል በአሰራር ሂደት ዋና ተከሳሽ ያወጡትን (**መጠን እንዲመለስ/reimbursement amount**) ይሆናል። ለከሳሾች የሚከፈል ማንኛውም ገንዘብ በፍርድ ቤቱ ዘንድ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት፤

(c) የመፍትሄ ስምምነት መጠን ድምር የሚመዘዝን ለከሳሾች ከተከፈለ በኋላ እንደሆነ ከዚያም በመፍትሄ ስምምነት ላይ ለመሳተፍ ለሚመዘገቡት የቡድን አባላት ይከፋፈላል። እያንዳንዱ ተሳታፊ የጎልማሳ ቡድን አባል የመፍትሄ መጠን ክፍያን በእኩልነት ድርሻ ያገኛል። የህጻናት ቡድን አባላት (ከ16 ዓመት በታች የሆኑት እስከ ሐምሌ/ July 4 ቀን 2020 ዓ.ም. ድረስ) ከጎልማሶች ድርሻ 50% ያገኛሉ።

(d) ለአሰራር ሂደት የወጣ ሌሎች ወጪዎች፤ ለህጋዊ ወጪዎች እና ለመፍትሄ ስምምነት ገንዘብ ማከፋፈል ወጪዎች ጨምሮ, ***ከመፍትሄ ስምምነት ገንዘብ*** አይቀነስም። እነዚህ ወጪዎች, የከሳሾች ህጋዊ ወጪዎችን ጨምሮ (በፍርድ ቤቱ እንደጸደቀ) በተከሳሹ በኩል ይከፈላሉ።

የመፍትሄ ስምምነት ገንዘብ አከፋፈልና ስርጭት ሂደት ከዚህ በታች በ6 ይገለጻል።

ከሳሾችና የቡድን አባላት የመፍትሄ ስምምነት ሂደቱን ለመክፈል ሲሉ ተከሳሹን በቀን 24 መስከረም/September 2021 ዓ.ም የተሻሻለው አዋጅ ላይ በተገለጸው መሠረት ከክሱ ይለቃሉ። በ27 ጥር/January 2022 ዓ.ም. በሰጡት መልስ፣ እንዲሁም ከአሰራር ሂደት ጉዳይ ወይም ተመሳሳይ ሁኔታ ጋር በተያያዘ ወይም ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ ወይም የሚነሱ አቤቱታዎች በሙሉ (**ጥያቄዎች/Claims**)።

## 5. ለታቀደው ስምምነት ውሳኔ ተቀባይነት ለማግኘት የሚደረገው ሂደት ምንድን ነው?

ከላይ በ4 ላይ እንደተገለጸው የቀረበው መፍትሄ ውሳኔ ተግባራዊ የሚሆነው ፍርድ ቤቱ ከፈቀደለት ብቻ ነው። የቀረበውን መፍትሄ ስምምነት ውሳኔ ስለመጽደቅ የሚለውን ለመወሰን ፍርድ ቤቱ የቀረበው ውሳኔ ፍትሃዊና ምክንያታዊ እንዲሁም ለጠቅላላው የቡድን አባላት ጥቅም እንጂ ለከሳሾች ብቻ የሚጠቅም መሆን አለመሆኑን ይመለከታል። ይህ የመፍትሄ ስምምነት ውሳኔ እንዲጸድቅ ሐምሌ/July 24 ቀን 2023 በቪክቶሪያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይካሄዳል። የቡድን አባላት በዚህ ፍርድ ችሎት ላይ የመገኘት መብት አላቸው።

እርስዎ የቡድን አባል ሊሆኑ እንደሚችሉ ከተሰማዎት እና ለመሳተፍ የሚፈልጉ ከሆነ፣ ከቀረበው የመፍትሄ ስምምነት ውሳኔ ሃሳብ አውጫ ውጡ ወይም ከመቃወም፣ ፍርድ ቤቱ ባዘዘው መሰረት ከተወሰኑ ቀናት ***በፊት*** እርምጃ መውሰድ አለባችሁ። የሚወስዱት እርምጃዎችና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ የጊዜ ገደብ ከዚህ በታች በ7 ተገልጿል።

## 6. የመፍትሄ ማስገኛ ጠቅላላ ገንዘብ አከፋፈል አሰራር ሂደቱ ምንድ ነው?

የቀረበው መፍትሄ ውሳኔ በፍርድ ቤቱ ዘንድ ተቀባይነት ካገኘ በከሳሽና በተከሳሽ መካከል በተስማማውና በፍርድ ቤቱ በተደነገገው መሠረት ለከሳሾችና ለቡድን አባላት ይከፋፈላል (**ለመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ አከፋፈል አሰራር**)። ፍርድ ቤቱ ለአንድ አስተዳዳሪ ይሾማል፡

(a) በመፍትሄ ማስገኛ አከፋፈል መርሐ ግብር መሰረት በቡድን አባላት በኩል የቀረቡትን ጥያቄዎች እንደሚገመግሙ፤ እና

(b) ከመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ መጠን ጥያቄ ከቀረበበት ጊዜ ለቡድን አባላት ክፍያ ይደረጋል።

ከሳሽና ተከሳሽ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጸሀፊ፣ ለፕሮፌሰር ዩዋን ዋላስ አም Professor Euan Wallace AM **አስተዳዳሪ** ተብለው እንዲሾሙ ፍርድ ቤቱ ፈቃድ ለመጠየቅ ተስማምተዋል። አስተዳዳሪው ተገቢውን ጥንቃቄና ክህሎት እንዲሁም በቡድን አባላት በአጠቃላይ ጥቅም እንጂ ለማንኛውም ግለሰብ የቡድን አባል ተወካይ በመሆን በመልካም እምነት የመፍትሄ ማስገኛን ገንዘብ ያከፋፍላል።

የመፍትሄ ማስገኛ ስርጭት መርሐ ግብር በአንቀጽ 8 ላይ ለስርጭት የሚሆን ቀመር ያስቀምጣል።

የመፍትሄ ማስገኛ ማከፋፈያ መርሐ ግብር ቅጅ ከዚህ በታች እና በኦንላይን ኢንተርኔት health.vic.gov.au/covid-19-towers ላይ ይገኛል።

## 7. የቡድን አባላት ምን እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ?

ለዚህ ማሳሰቢያ ምላሽ ለመስጠት ሊወስዱት የሚችሉት ሶስት እርምጃዎች አሉ። እነዚህ ተግባራት ከዚህ በታች በዝርዝር ተዘርዝረዋል። ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሰነዶች የተተረጎሙ ቅጆዎች ከፈለጉ ከቀን 10 ግንቦት/May 2023 ዓ.ም ጀምሮ ማግኘት የሚችሉት፡

| | |
|---|---|
| *በኦንላይን መስመር ላይ:* | health.vic.gov.au/covid-19-towers; እና<br>www.clemenshaskin.com; |
| *ጽሁፍ ወረቀት/ሃርድ ኮፒዎች* | የከሳሽ ህጋዊ ተወካዮች፤ እንዲሁም በእስቴት ህንጻዎች<br>የሚገኙ አስተዳደራዊ ቢሮዎች፡ |

ኖርዝ ሜልቦርን የመኖሪያ ቤት ቢሮ አድራሻ 33 Alfred Street North Melbourne,
**ስልክ** (03) 9326 6377

አስኮት ቫሌ መኖሪያ ቤት ቢሮ
አድራሻ፡ 12 Churchill Avenue, Ascot Vale
**ስልክ**: (03) 9371 6200

**ምርጫ 1:** **በቀረበው የመፍትሄ ስምምነት ላይ ለመሳተፍ ይመዝገቡ**

እርስዎ ከአሰራር ሂደት ጋር በተያያዘ የገንዘብ ካሳ መቀበል ከፈለጉ በቀረበው የመፍትሄ ስምምነት ላይ ለመሳተፍ መመዝገብ **አለብዎት**።

በቀረበው የመፍትሄ ስምምነት ላይ ለመሳተፍ ለመመዝገብ በቀን **27 ሰኔ/June 2023** ዓ.ም **"የአቤቱታ ማስታወቂያ"** ቅጽን ሞልተው ማቅረብ አለብዎት።

የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅጽን እንደሚከተለው ማጠናቀቅ ይችላሉ፡

(a) በኦንላይን መስመር health.vic.gov.au/covid-19-towers ላይ የሚገኘውን የኢንተርኔት ቅጽ ማስገባት፤ ወይም

(b) ይህን የማስታወቂያ ጥያቄ በ Annexure B የማስረከቢያ ቅጽ ማጠናቀቅ እና ወደ አስተዳዳሪው በመመለስ፡

i. በኢሜል ለ: COVID-19-Towers@health.vic.gov.au;

ii. በፖስታ:
አድራሻ COVID-19 Towers
50 Lonsdale St
Melbourne Victoria 3000; ወይም

iii. ለማድረስ በአድራሻ:
COVID-19 Towers
50 Lonsdale St
Melbourne Victoria 3000

አስተዳዳሪው በቀረበው መፍትሄ ውሳኔ ላይ ለመሳተፍ የሚመዘገቡ ሰዎችን ጥያቄ ይመለከታል። የቀረበው መፍትሄ ስምምነት ተቀባይነት ካገኘና አስተዳዳሪው የተመዘገበ ሰው የቡድን አባል መሆኑን ከወሰነ፣ ከመፍትሄ ማስገኛ ድምር ውስጥ የተከፈለ ክፍያ ለዚያው ግለሰብ በመፍትሄ ማስገኛ አከፋፈል መርሐ ግብር መሠረት ይደረጋል።

ለአስተዳደሪው የአቤቱታ ማስታወቂያ ቅጽ በማቅረብ፣ አስተዳዳሪው ከመፍትሄ ማስገኛ የገንዘብ ካሳ ለማግኘት ብቁ መሆንዎን ለመወሰን የመፍትሄ ማስገኛ ስርጭት መርሐ ግብርን ተግባራዊ እንደሚያደርግ ይስማማሉ። የአስተዳዳሪው ብቃትዎን ወይም እድሜዎን በነጻ መገምገም ይፈልጋል። ነገር ግን ከአቤቱታዎች ወይም ከአስተዳዳሪው የአቤቱታ ቅጽ ግምገማ ጋር በተያያዘ ህጋዊ ሂደቶችን መጀመር አይቻልዎትም።

**ምርጫ 2:** **ከቀረበው መፍትሄ ስምምነት ውሳኔ አውጣና በአሰራር ሂደቱ ውስጥ የቡድን አባል መሆንዎን ማቆም።**

በአሰራር ሂደቱ ውስጥ የቡድን አባል መሆንን "መምረጥ" የሚለውን በመምረጥ ሊታቆም ትችላለህ። ከአሰራር ሂደቱ ብትወጣ የማትታገድበት በቀረበ የመፍትሄ

ስምምነት እና እርስዎ ምስረታ ከመፍትሄ ማስገኛ ገንዘብ ስርጭት ለመቀበል ብቁ እንዳልሆኑ ነው። ከቡድኑ አባላት ጋር በተያያዘ የራሳቸውን ነጻ የፍርድ ሂደት መጀመር ይችላሉ።

ፍርድ ቤቱ ቀደም ሲል ከችሎቱ ለመውጣት የወሰነው የጊዜ ገደብ ሐምሌ/July 1 ቀን 2022 ዓ.ም ነበር። ከዚያ ቀን በፊት "የመውጫ ማሳሰቢያ" ያቀረበ ማንኛውም ሰው ቀድሞውኑ እንደወጣ ነው።

***ከአሰራር ሂደቱ መውጣት የምትፈልግ ከሆነ፡-*** ፍርድ ቤቱ የቀጠሮው ጊዜ ቢያልፍም እንኳ እንድትመርጠው የመፍቀድ ሥልጣን አለው። ፍርድ ቤቱ ይህን እንድትመርጡ እንዲፈቅድላችሁ ከፈለጉ፣"የማመልከቻ ውይይት በአንድ ቡድን አባል የተደነገገውን ጊዜ ለማራዘም የማመልከቻ ማስታወቂያ" የሚል ርዕስ ያለውን ቅጽ ማጠናቀቅ አለባችሁ።

ከላይ የተጠቀሰውን ማስታወቂያ በዚህ ማሳሰቢያ Anxure C ወይም በኦንላይን ኢንተርኔት health.vic.gov.au/covid-19-towers ላይ በማጠናቀቅ እና በማስታወቂያው አድራሻ ላይ በቀን 29 ግንቦት/May 29 2023 ዓ.ም በፖስታ ወይም በኢሜይል ወደ ቪክቶሪያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመመለስ ከላይ ያለውን ማስታወቂያ ማጠናቀቅ ይችላሉ።

***ቀደም ሲል ከመረጡ እንደ ቡድን አባል መሆንዎ ለመመለስ የሚፈልጉ ከሆነ፡-*** ፍርድ ቤቱ የቡድን አባል እንዲሆኑ የማስመለስ ስልጣን አለው። ፍርድ ቤቱ በቡድን አባልነት ወደነበሩት ለመመለስ እንዲያስብበት የሚፈልጉ ከሆነ እስከ ቀን 29 ግንቦት/May 2023 ዓ.ም ድረስ "የቡድን አባል እንደገና መቢያ ማስታወቂያ" ማጠናቀቅ አለብዎት። ይህንን ማሳሰቢያ በAnnexure D ቅጽ በኦንላይን ኢንተርኔት health.vic.gov.au/covid-19-towers አድርጎ መሙላት እና ፎርሙ ላይ ባለው አድራሻ ላይ በፖስታ ወይም በኢሜይል ወደ ቪክቶሪያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመመለስ የመልሶ ማቋቋምን ማጠናቀቅ ይችላሉ።

***አስቀድመው የወሰኑ መሆን አለመሆንውን እርግጠኛ ካልሆኑ፡-*** የከሳሽ ህጋዊ ተወካይ ክሌመንስ ሃስኪን ሌጋልን/ Clemens Haskin Legal በማነጋገር የወሰዱት መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይችላሉ።

**ምርጫ 3** **በቀረበው የመፍትሄ ስምምነት ላይ ተቃውሞ**

የቡድን አባል ከሆኑ ፍርድ ቤቱ የቀረበውን መፍትሄ ውሳኔ ሊቀበለው ይገባል በሚለው ሀሳብ መስማማትዎን ወይም አለመስማማትዎን ለመናገር ለፍርድ ቤቱ የማስገባት መብት አለዎ።

ፍርድ ቤቱ የቀረበውን መፍትሄ ውሳኔ መቀበል የለበትም ብለው የሚያስቡ ከሆነ "የተጠየቀውን ውሳኔ የመቃወሚያ ማስታወቂያ ቅጽ" በማጠናቀቅ ተቃውሞ ማቅረብ ይችላሉ። የተቃውሞ ማቅረቢያ ማሳሰቢያን በዚህ Annexure E ቅጽ መሙላት ማጠናቀቅ ወይም በኦንላይን ኢንተርኔት ላይ health.vic.gov.au/covid-19-towers ማካሄድ እና ማሳሰቢያውን በአድራሻው ወደ ቪክቶሪያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመመለስ የክስ ማስታወቂያውን ማጠናቀቅ ይችላሉ።

ማንኛውም የመቃወሚያ ማስታወቂያ እስከ ግንቦት/May 29 ቀን 2023 ዓ.ም ድረስ ለፍርድ ቤት መቅረብ አለበት። ያለዎትን ተቃውሞ የሚደግፍ ማስረጃ ወይም በጽሑፍ የሰፈረ መግለጫ ሀሳብ ማቅረብ ከፈለጉ እስከ ሰኔ/June 13 ቀን 2023 ድረስ ለፍርድ ቤቱ ማቅረብ አለብዎት።

ፍርድ ቤቱ ሐምሌ/July 24 ቀን 2023 በተካሄደው ፍርድ ችሎት ላይ የቀረበውን መፍትሄ ውሳኔ ተቀባይነት ከመስጠቱ በፊት በቡድን አባላት የተጠናቀቁትን የተቃውሞ ማስታወቂያዎችን በሙሉ በሰዓቱ ይመለከታል ።

የታቀደውን መፍትሄ ስምምነት መቃወም ይችላሉ *እንዲሁም* አማራጭ 1'ን ወስደው በታቀደው ስምምነት ላይ ለመሳተፍ መመዝገብ ነው።

አማራጭ 2'ን ወስደው ከታቀደው የመፍትሄ ውሳኔ ሃሳብ ከወጡ የታቀደውን መፍትሄ ስምምነት እንደተቃወሙ ይቆጠር ይሆናል።

ከላይ ከተገለጹት ተግባራት መካከል አንዳቸውንም ካልወሰዱና ለዚህ ማሳሰቢያ ምላሽ ለመስጠት ምንም ዓይነት እርምጃ ካልወሰዱ ፍርድ ቤቱ ሌላ ውሳኔ እስካልሰጠ ድረስ በቀረበው ውሳኔ ላይ የመሳተፍ መብት አይኖርዎትም። በዚህም መሰረት ምንም ካላደረጉና ካላሰሩ የቀረበው የመፍትሄ ውሳኔ ከጸደቀ ታዲያ አስተዳዳሪው የጠየቁትን ነገር መገምገም አይችሉም። ስለዚህ በመፍትሄ ማስገኛ መጠን ገንዘብ ላይ የመከፋፈል መብት አይኖርዎትም። በተጨማሪም በተጠየቀው መፍትሄ ስምምነት ጋር እንደሚጣመሩ እና ተከሳሹን በተመለከተ ክስ ማቅረብ አይችሉም።

## 8. ለልጆች ቅጽ ማጠናቀቂያ፤ በአካል ጉዳተኛ ስር ላለ እና እራሳቸውን መንከባከብ ለማይችሉ ሌሎች ሰዎች ይሆናል።

በቀን 27 ሰኔ/June 2023 ዓ.ም እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ካሉዎት እና መመዝገብ የምትፈልጉ (ምርጫ/Option 1) በማሳሰቢያ ክስ ቅጽ ላይ ያለዎትን ዝርዝር መረጃ በቅጹ ውስጥ ማካተት ይኖርብዎታል። የተለያየ የአቤቱታ ማቅረቢያ ቅጾችን መሙላት የለባቸውም።
ከአሰራር ሂደቱ (አማራጭ/Option 2) ለመውጣት ማመልከት የሚፈልጉ ከሆነ፤ ለእያንዳንዱ በቡድን አባል ቅጽ ፎርም የተዘጋጀውን ጊዜ ለማራዘም የተለየ ማመልከቻ ማጠናቀቅ ያስፈልግዎታል። ማንኛውም ተቃውሞ (አማራጭ/Option 3) በወላጁ ወይም በሞግዚቱ አማካኝነት ለልጁ ሊቀርብ ይችላል።

የሚንከባከብዎ ሞግዚት ጠባቂ ወይም የግል ተወካይ ካለዎት ወይም በአካል ጉዳተኛ ስር ከሆኑ እነዚህን ሰነዶች እንዴት ማካሄድ እንዳለብዎት ለመወሰን እንዲረዷችሁ ወደ እነሱ ማስተላለፍ ይኖርብዎታል።

## 9. ስለታቀደው መፍትሄ ስምምነት ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት ይችላሉ?

ስለቀረበው መፍትሄ ስምምነት ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ አግባብነት ያላቸውን ሰነዶች ቅጂዎችን ማግኘት ይችላሉ። ይህም ከአስተዳዳሪው ድህረገጽ health.vic.gov.au/covid-19-towers ወይም ከከሳሾቹ የክሌመንስ ሃስኪን የሕግ/ Clemens Haskin Legal ተወካዮች ድህረገጽ፣ www.clemenshaskin.com ላይ ይሆናል።

እባክዎ ከላይ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በጥንቃቄ ግምት ውስጥ ማስገባት። እርስዎ የቡድን አባል መሆንዎን እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም ስለሚወስዱት እርምጃ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ከፈለጉ፤ ክሌመንስ ሃስኪን ህጋው/ Clemens Haskin Legal በስልክ (03) 9988 5035 ወይም ኢሜይል info@clemenshaskin.com, ወይም የእራስዎን የህግ ምክር አቅራቢ መጠየቅ አለብዎት።

ይህ ማስታወቂያ የሚታተመው የቪክቶሪያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሚያዝያ/April 20 ቀን 2023 ባወጣው ትእዛዝ መሠረት ነው።